# የእኩል ተጠቃሚነት መርህ ከአገራችን ፖሊሲ አንፃር

ስሜነህ 09-26-17

ኢትዮጵያ ባዘጋጀችው እና ላሳለፍናቸው በአስራዎቹ የሚቆጠሩ አመታት በስራ ላይ በቆየው የውጭ ግንኙነትና አገራዊ ደኅንነት ፖሊሲ ላይ፣ እያንዳንዱን አጎራባች በተለይ ጎረቤት አገሮችን ጨምሮ ምን ዓይነት ፖሊሲ እንደምትከተል፣ ምን ዓይነት ፀጋዎች እንዳሉ፣ ተግዳሮቶቹ ምን እንደሆኑ በደንብ ተለይቶ መቀመጡ ይታወቃል። በኢትዮጵያ ማዕከል ወደ ዘጠኝ የሚጠጉ ሃገራት መኖራቸውም በተመሳሳይ ይታወቃል፤ ፑንትላንድንና ሶማሌላንድን እንደ አገር ከወሰድናቸው ማለት ነው። እነዚህ ሁሉም አገሮች ደግሞ ከአንድና ከሦስት በላይ ወደቦች አሏቸው። ለምሳሌ ሶማሊያ ብቻዋን የአሥር ወደቦች ባለቤት ናት። ኢትዮጵያ ደግሞ ወደብ አልባ ሃገር ናት። ስለሆነም ኢትዮጵያ ለብዙ ጊዜ ከጂቡቲ የወደብ አገልግሎት ስትጠቀም ቆይታለች። አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የጂቡቲ የወደብ አገልግሎት ሽፋን የሰፋ መሆኑ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአገልግሎት ላይ ክፍተቶች ስለመኖራቸው ተገልጋዮች በተለይም አስመጪዎችና ላኪዎች በተደጋጋሚ ከማንሳታቸው ጋር ተያይዞ ኢትዮጵያ እንደ ስትራቴጂ በሁሉም ጎረቤት አገሮች ያሉትን ወደቦች በእኩል ደረጃ የመጠቀም መርሆን መከተሏ ተገቢ ይሆናል።

ይህ ማለት ግን የሰጪና ተቀባይ መርህ ሳይሆን የእኩል ተጠቃሚነት መርህ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። እነዚህ አጎራባች የሆኑ የቀጠናው ሃገራት ያላቸው ወደብ ነው። መርሁ የእነዚህን ሃገሮች ወደብ ኢትዮጵያ ካልተጠቀመች ሊጠቀም የሚችል የሌለ ከመሆኑ የሚመነጭ ነው። በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገት ከጎረቤት አገሮች ጋር ባለው የኢኮኖሚ ትስስር የሚለካ ነው። ኢትዮጵያ ኢኮኖሚዋ በጣም ካደገና የወደብ ፍላጎቷ በጨመረ ቁጥር የአገሮችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ይጨምራል የሚለው ነው መርሁ። በዚህ ረገድ ለተወሰነ ጊዜ ሙሉ በሙሉ በጂቡቲ ላይ ብንቆይም፣ አሁን በሁሉም አገሮች ላይ የወደብ አገልግሎትን ማስፋት እንደ ስትራቴጂ እየታየ ለመሆኑ የባለፈው ወር የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሱዳን ጉብኝት እና የሁለትዮሽ ስምምነቶች አመላካች ናቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ ፍላጎት ሁል ጊዜ ገደብ የሌለው የመሆኑ ምጣኔ ሃብታዊ እውነታም ሊዘነጋ አይገባም። በዚህ እውነታ ምክንያት ጂቡቲ 90 በመቶ በወደቦቿ ብንጠቀም ደስታዋ እንደሚሆን አያጠያይቅም። ሱዳንም እንዲሁ።ሁሉም አገሮች የኢኮኖሚ ጥቅማቸውን ከፍ የማድረግ ፍላጎት ያላቸው መሆኑ አያከራክርም።ዋናው ጉዳይ የኢኮኖሚ ጥቅማቸውን ማሳደግ ስለሆነ አሁን ኢትዮጵያ ከምትከተለው መርህ አንፃር የተጣጣመ መሆኑ ነው። ቀጣናዊ ትስስርና ውህደት ከሚገለጽባቸው አንዱ የመሠረተ ልማት ትስስር ነው።

የኢኮኖሚ ትስስሩ መጨረሻ ላይ ሁሉን አቀፍ ወደ ሆነ ፖለቲካዊ ትስስር ማምራት ነው። ይህ ደግሞ የምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግሥታት (ኢጋድ) ካስቀመጠው መርህ አንፃርም አንዱ አቅጣጫ ነው። የአፍሪካ ኅብረት ለ2063 ካስቀመጠው መርህ አንፃርም ኢትዮጵያ እየሄደችበት ያለው አቅጣጫ ከዚያ ጋር ተያይዞ ሊታይ የሚችል ነው። በዋናነት በቀጣናው ሰላም ማምጣት፣ ልማት ማምጣት፣ ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነትና ፍትሐዊ የሆነ የሀብት አጠቃቀም አቅጣጫን ነው ሃገራችን የምትከተለው።

እነዚህ ምክንያታዊና ከአህጉር አቀፍ እና አለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘቡ መርሆዎች ባሉበት ሁኔታ የጠቅላይ ሚንስትሩን የሱዳን ጉብኝት ተከትሎ ኢትዮጵያ ፊቷን ወደ ሱዳን ማዞሯ ተገዳ ነው የሚሉ ወገኖች የተደመጡ ሲሆን፤ በተለይ በዓባይ ዲፕሎማሲ ሱዳን ከኢትዮጵያ ጎን እንድትቆም ለማግባባት ነው በሚል በግብጽ ላይ የተቀዳጀነውን ዲፕሎማሲያዊ የበላይነት ለማኮላሸት የሚተጉ ሃይሎች እየተደመጡ ነውና እውነታው ላይ በምክንያት መሟገት ስለታላቁ የህዳሴ ግድባችን እውንነት ተገቢ ይሆናልና ነው አጀንዳውን ማንሳቴ።

በመሰረቱ ኢትዮጵያና ሱዳን በሰጥቶ መቀበል መርሆዎ ስለፍትሃዊ ተጠቃሚነት በዓባይ ጉዳይ ላይ አንድ ዓይነት አቋም የያዙት ኢትዮጵያ ፖርት ሱዳንን መጠቀም ሳትጀምር ነው። ስለሆነም ገና ከመነሻው በዚህ አመክንዮ ብቻ የጠቅላይ ሚንስትሩ ጉብኝት በዋናነት ከላይ ለተመለከቱት ምጣኔ ሃብታዊ ጉዳዮች  ብቻ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። አባይ ከሆነም የእግረ መንገድ አጀንዳ ካልሆነ በስተቀር ጉዳዩ አስቀድሞ ተቋጭቷል። ባይሆን ምጣኔ ሃብታዊው ጉብኝትና ስምምነት ባይሆን ከሱዳን ጋር ተመሳሳይ አቋም በተያዘበት አጀንዳ ላይ በሃገራቱ መካከል የበለጠ መተማመኑን ያጠናክረዋል ቢባል ምክንያታዊና ጤናማ ምልከታ ይሆናል።

በሌላ አመክንዮ ጉዳዩን ስንመለከተውም በሱዳን በኩል ኢትዮጵያን ሊያስገድድ የሚችል አንዳች ነገር አይችልም። የዓባይ ውኃ ፍትሐዊ አጠቃቀም ሲባል ሁሌም መዘንጋት የሌለበት ነገር አለ። ይኸውም ግብጽና ሱዳንን ብቻ ስለአባይ የመመልከት ጉዳይ ነው። ዓባይ ተፋሰስ ውስጥ ወደ አሥር አገሮች መኖራቸውን ታሳቢ ያደረገ ምልከታ ብቻ ነው ምክንያታዊ የሚሆነው። በዚህ ቅኝት ጉዳዩን ካየነው የምናገኘው መልስ የታላቁ የህዳሴ ግድብ ጠቀሜታ ለሱዳንና ኢትዮጵያ ወይም ለግብጽና ኢትዮጵያ  ብቻ አለመሆኑን ነው። ከታላቁ ግድብ የሚገኘው ትሩፋት ለሁሉም ጎረቤት አገሮች የሚከፋፈል ሀብት ነው። ለዚህም ነው ካምፓላ ላይ የተደረሰው ስምምነት ሁሉም አገሮች ያላቸውን ተፈጥሮ ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መጠቀም አለባቸው የሚለው። ስለዚህ ግድቡ ለኢትዮጵያ ብቻ አይደለም ለሱዳንም፣ ለግብፅም፣ ለሌሎቹም የተፋሰስ ሃገራቱ ጠቃሚ ስለሚሆን ያለአንዳች መንገራገጭ እየተገነባ ያለው። በሌላ በኩል ሱዳን ያላት ሀብት ወደብ ነው። ኢትዮጵያ ደግሞ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የወደብ አገልግሎት ከጎረቤት አገሮች ለማግኘት መስራቷ ተገቢና ምክንያታዊ ነው። ስለሆነም ኢትዮጵያን ወደሱዳን የገፋት አሁን በወቅቱ በሱዳን የተመቻቸው ሁኔታ እንጂ ኢትዮጵያን ሊያስገድድ የሚችል ሁኔታ ተፈጥሮ ሊሆን የሚችልበት አመክንዮ የለም። ኢትዮጵያ፣ ግብፅና ሱዳን ካርቱም ውስጥ የደረሱበት ስምምነት አንዳችን የሌላችን ጉዳት ሳንፈልግ ያለንን ፀጋ በእኩል ደረጃ እንጠቀማለን በሚል በተደመደመበት ሁኔታ ሱዳንና ኢትዮጵያ ለብቻቸው በጓዳ ሊሸርቡ የሚችሉት ሴራ አይኖርም፤ ቢሸርቡም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች ወንዝ የማያሻግር ሸረባ ነው የሚሆነው።

ሌሎች ምክንያታዊ ምክንያቶችንም ማንሳት ይቻላል። በህዳሴ ግድቡ ሱዳን ብቻዋን ወሳኝ ወይም ቁልፍ አገር ልትሆን የምትችልበት እድልና ህጋዊ መሰረት የለም። ሌላው ቀርቶ አሁን ያለው ማዕቀፍ የሚያመላክተው 85 በመቶ የአባይ ምንጭ የሆነችው ሃገረ ኢትዮጵያም ብቻዋን ወሳኝ አይደለችም። ሁሉም የተፋሰስ አገሮች እኩል ሚና ነው ያላቸው። በእርግጥ ቀደም ሲል የነበረው እ.ኤ.አ የ1959 እና የ1929 ስምምነት ግብፅን ወሳኝ አገር አድርጎ ያስቀመጣት መሆኑ ይታወቃል። ካምፓላ ላይ እ.ኤ.አ በ2010 የተደረሰው ስምምነት ግን ይህን በመሰረቱ የቀየረ እና የሁሉንም ተፋሰስ ሃገራት ተጠቃሚነት ያረጋገጠ ነው። ስለዚህ ማንም አገር ብቻውን ወሳኝ እንዳይሆን የሚያደርግ ስምምነት ባለበት ሁኔታ ሱዳንና ኢትዮጵያን አቆራኝቶ ነገር ለማደፍረስ መሞከር የትም የማያደርስና ዝም ብሎ ነገር የመቆስቆስ የጭር ሲል አልወድም አባዜ ነው።

ዋናው ነገር ኢትዮጵያ መጀመርያ የቤት ሥራዋን ጥንቅቅ አድርጋ መጨረሷ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉንም እኩል የሚያደርግ ሥርዓት ተገንብቷል። የዚህ ዋነኛ ማጠንጠኛው ደግሞ ሕገ መንግሥቱ ነው። በእርግጥ ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ክፍተቶች እዚያም እዚህም ይታያሉ። በቅርቡ የተከሰቱና ወደግጭት ያመሩ ጥያቄዎችም ምንጫቸው ሕገ መንግሥቱን በትክክል ወደ መሬት ካለማውረድ ጋር የተያያዙ ነገሮች ናቸው። ሕገ መንግሥቱን ካለመረዳትና ያለውን ጠባይ በሚገባ ካለመገንዘብ ጋር ተያይዘው የመጡ ችግሮች ናቸው። ሕገ መንግሥቱ ላይ የተቀመጡ ነገሮች በትክክል ወደ መሬት ሲወርዱ ሁሉም ችግሮች ይፈታሉ። ስለሆነም የሚቀረን ነገር ቢኖር ሁሉም ሰው ስለሕገ መንግሥቱ ያለውን ግንዛቤና ዕውቀት ከፍ የማድረግ ጉዳይ ነው።

ስለታላቁ የህዳሴ ግድባችን ፍጻሜ ከሕገ መንግሥቱ ቀጥሎ እያንዳንዱ ሰውና መንግሥት መሥራት የሚገባው የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነትና አገራዊ ደኅንነት ፖሊሲው ላይ ነው። ከሕገ መንግሥቱ ቀጥሎ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ፣ እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በዚህ ላይ ግልጽ የሆነ ግንዛቤና መረዳት ሊኖረው ይገባል። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ህልውና የሚወሰነው ኢትዮጵያ ከሌሎች ጋር በምታደርገው ግንኙነት ስለሆነ። ለዘመናት የኢትዮጵያ ጠላቶች ከውጭ ሲመጡ የነበሩት የውስጥ ችግሮቿን በአግባቡ ማስተናገድ ባለመቻሏ መሆኑን መዘንጋት አይገባም። የውጭ ፖሊሲ ማለት ደግሞ ያለንን ነገር ወይም ፍላጎት ለሌላው የምንገልጽበት መንገድ ነው። ሌላው ዓለም እኛን የሚያይበት መነጽር ነው። የምንከተለው የውጭ ፖሊሲ የአንድን አገር ግንኙነት ጥንካሬና ጉድለት የሚያሳይ ነው። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ተገቢውን ሥራ መሥራት አለበት።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ ሁልጊዜ ራሷን ለመከላከል አሁን እያደረገችው እንዳለው አቋሟን ጠንካራ ማድረግ አለባት። የተጋላጭነት ደረጃዋን እጅግ ዝቅ ማድረግ አለባት። በታሪክ አጋጣሚ ሁሉንም ኢትዮጵያ ላይ የተቃጡ ጦርነቶች ብናስታውስ ሁልጊዜ ኢትዮጵያ ያላትን ድክመቶች መጠቀሚያ ያደረጉ ናቸው። በዋናነት ደግሞ አሁን የተፈጠረው የፖለቲካ ሁኔታ መሠረት እንዲይዝ የፀረ ሙስና ትግሉ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት።

ኢትዮጵያ እስከ ዛሬ ድረስ ስትከተለው የነበረው በውስጥ ጉዳይ ላይ ማተኮር ነው። በዚሁ መሰረት ኢትዮጵያ በውስጥ ጉዳይዋ ላይ ትኩረት ማድረጓን አጠናክራ ከቀጠለች፣ በልማትና በዴሞክራሲ ጉዳይ ላይ ትኩረት ካደረገች፣ ኢኮኖሚዋን ካበለፀገችና ካሳደገች የኢኮኖሚ ትስስር ይኖራል፤ ለጎረቤቶቿ መልካም የገበያ አጋጣሚን፤ እንዲሁም ሰፊ የሥራ ዕድልን ይፈጠራል። ሌሎች ጎረቤት አገሮችም ከዚህ ትሩፋት ተጠቃሚ ይሆናሉ፤ *የእኩል ተጠቃሚነት መርህ* ስንልም ይሄንኑ ነው።